# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!



## ከግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የተሰጠ ልዩ መግለጫና ተግባሪዊ የመጀመሪያ እርከን የትግል ጥሪ

## ሁላችንም አንዳርጋቸው ጽጌዎች ነን! ! !

ሰኔ 29 ቀን 2006 ዓ.ም

በየጊዜው እየከረረና እየገረረ የመጣው ትግላችን "ሁላችን አንዳርጋቸው ጽጌዎች ነን" ወደ ተባለ አዲስ ምዕራፍ ተሸጋግሯል። ይህ ጽሁፍ የዚህን የትግል ምዕራፍ ምንነትና ይዘት በአጭሩ ያብራራል። በዚህ ጽሁፍ ላይ የሰፈሩት ዓረፍተ ነገሮች ተነበው የሚታለፉ ሳይሆን በተግባር የሚተረጎሙ ሥራዎች ናቸው።

አንዳርጋቸው ጽጌን መሆን ምን ማለት ነው? አንዳርጋቸው ጽጌ ለፍትህ፣ ለነፃነት፣ ለዲሞክራሲና ለእኩልነት በጀግንነት የቆመ፤ ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ሁሉ ሲከፍል የነበረና አሁንም እየከፈለ ያለ መሪያችን ነው። አንዳርጋቸው ጽጌን መሆን ማለት ልክ እንደሱ ትሁት ሆኖም ግን ቆራጥ፤ ሆደ ሰፊ በዚያው ልክ ደግሞ መራር፤ አስተዋይና ብልህ ሆኖም ተግባር ተኮር መሆን ማለት ነው። አንዳርጋቸው ጽጌን መሆን ማለት ወያኔን ለማስወገድ መደረግ የሚገባውን እርምጃ ለመውሰድ የተዘጋጀ ሰው መሆን ማለት ነው። አንዳርጋቸው ጽጌን መሆን ማለት ለአገርና ለትውልድ ቤዛ መሆን ማለት ነው።

ወያኔ፣ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ላይ ካተኮረባቸው ምክንያቶች አንዱ የወያኔን የዘር ፖለቲካና ፕሮፖጋንዳ በሚያመክን መልኩ በተግባር ትግል ውስጥ ካሉ የኦሮሞ፣ የአፋር፣ የኦጋዴን፣ የጋምቤላ እና ሌሎች ዘውግ ተኮር ድርጅቶች ጋር ንቅናቄዓችን ተግባራዊ ትብብር ማድረግ የሚችሉበት ደረጃ ድረስ ማቀራረብ የቻለ መሪ መሆኑ ነው። ከሁሉም በላይ ለወያኔ የጉሮሮ ቁስል የሆነበት ደግሞ ከትግራይ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ትህዴን) ጋር ግንቦት 7 የፈጠረው ጠንካራ ትብብር ነው። በትህዴን ጋር በመሆን አቶ አንዳርጋቸው ወያኔ በትግራይ ሕዝብ ጀርባ መንጠልጠል እንዳይችል አድርጎታል። እናም አንዳርጋቸው ጽጌን መሆን ማለት ከዘረኝነት ፀድቶ መገኘት ማለትም ጭምር ነው። አንዳርጋቸው ጽጌን መሆን ማለት በኢትዮጵያዊያን እኩልነት እና እኩል ባለመብትነት ከልብ ማመን እና ለእኩልነት በጽናት መታገል ማለት ነው።

አንዳርጋቸው ጽጌን ለመሆን የግድ የግንቦት 7 አባል መሆንን አይጠየቅም። አንዳርጋቸው ጽጌን ለመሆን ለመልካም ዓላማዎች መሳካት ዋጋ ለመክፈል መዘጋጀትን እንጂ የግድ ከአንድ ወይም ከሌላ ድርጅት ጋር መወገንን አያሻም። ያም ሆኖ ግን አንዳርጋቸው ጽጌን የሆነ ሰው በጠንካራ ድርጅት የታገዘ ትግል አስፈላጊነት ይረዳል።

በመጨረሻም አንዳርጋቸው ጽጌን መሆን አኪሎ አኳኝ፣ አንዱዓለም አራጌ፣ ርዕዮት ዓለሙ፣ እስክንድር ነጋ፣ በቀለ ገርባ፣ ኦልባና ሌሊሳ እና እዚህ ዘርዝረን ልንጨርሳቸው የማንችላቸው ጀግኖቻችንን ሁሉ መሆን ማለት ነው።
"የሁላችንም አንዳርጋቸው ጽጌዎች ነን" ዘመቻ ትኩረቶችን በየጊዜው የምንገልጽ ሲሆን ከነገ ጀምሮ በሥራ ላይ መዋል ያለበት የዓለም ዓቀፍ ዘመቻው የመጀመሪያ እርከን ትኩረቶች በዚህ በታች ቀርበዋል።

### የዘመቻው የመጀመሪያው እርከን ትኩረቶች

ይህ የመጀመሪያ እርከን ሶስት ቦታዎች ላይ ያተኩራል፡- የመን፣ ብርታኒያ እና ወያኔ

### የመንን በተመለከተ

የየመን መንግሥት የዓለም ዓቀፍ ህግም ሆነ የየመን የራሷን ህግ በመተላለፍ መሪያችንን ለእርድ አሳልፎ ሰጥቶብናል። ከመጀመሪያው ጀምሮ ለየመን መንግሥት የተደረገው ተማጽኖ ሰሚ ጆሮ አላገኘም። እስካሁንም ድረስ የየመን መንግሥት አቶ አንዳርጋቸውን ማሠሩና ለወያኔ አሳልፎ መስጠቱ በይፋ አላመነም። እኛ ባለን መረጃ መሠረት በአይሮፕላን ማረፊያው ከማገት ጀምሮ በልዩ በረራ ወደ ኢትዮጵያ እስከ መላክ ድረስ ያለውን የውንብድና ሥራ በየመን በኩል ሆኖ የሠራው ቀጥታ ተጠሪነቱ ለየመን ፕሬዚዳንት የሆነው የስለላ ድርጅት ነው። በዚህም ሳቢያ የየመን መንግሥት ሊቀለበስ የማይችል እና በቀላሉ የማይፋቅ ታሪካዊ ስህተት ፈጽሟል። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የመን አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ለወያኔ ፋሽስቶች አሳልፋ መስጠቷን በማስመልከት የወጣ መግለጫ

ሰኔ 27 ቀን 2006 ዓ.ም

የግንቦት 7፣ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ዋና ፀሐፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓም ለሥራ ጉዳይ በየመኒያ አየር መንገድ አይሮፕላን ተጉዞ በትራንዚት ሰንዓ ከተማ እያለ በየመን መንግሥት ፀጥታ ኃይሎች በሕገወጥ መንገድ ታግቶ መቆየቱ ማስታወቃችን ይታወሳል።

የየመን መንግሥት በህገወጥ መንገድ ያገተብንን የንቅናቀዓችንን አመራር በአስቸኳይ እንዲፈታ በተለያዩ መንገዶች ላለፈው አንድ ሣምንት ያደረግነው ጥረት አልተሳካም። የአገሩን የረዥም ጊዜ ጥቅም ማየት የተሳነው የየመን መንግሥት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ይልቅ አምባገኑን ወያኔ መርጦ መሪያችንን ለእርድ አሳልፎ ሰጥቶብናል። በዚህም ሳቢያ የየመን መንግሥት ይቅርታ የማያሰጥ፤ ዘመን የማይሽረው ታሪካዊ ስህተት ፈጽሟል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለወዳጅ ጎረቤት ትሁትና ቀና ቢሆንም ጥቃት በሚያደርስበት የቅርብም ሆነ የሩቅ ጎረቤት ላይ ግን ቁጣውን የሚመጥን የአፀፋ እርምጃ መውሰድ ያውቅበታል።

የወያኔ ፋሽስቶች አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን በማሰቃየት ትግላችንን ማቀዝቀዝ እንደማይችሉ ልናረጋግጥላቸው እንወዳለን። እንዲያውም በግልባጩ ቁጣና እልሃችን በእጥፍ ድርብ በመጨመር ትግላችንን ያጦዘዋል። ወያኔ፣ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን በውንብድና ጠልፎ መውሰዱ የትግሉን ሜዳ አስፍቶታል፤ የትግሉንም ዓይነት አብዝቶታል። ይህ ደግሞ የወያኔ ፋሽስቶችን ከፍ ያለ ዋጋ ያስከፍላቸዋል። ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## አንዳርጋቸው የማይጨበጥ ጽኑ መንፈስ እንጂ አንድ ግለሰብ አይደለም!!!

የግንቦት 7 ሕዝባዊ ሃይል

በኢትዮጵያ ዘመናዊ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ከታዩ አርቆ አሳቢ፣ አስተዋይና ብልህ ፖለቲከኞች አንዱ የሆነው ታላቁ የነፃነት ታጋይ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ለሥራ ጉዳይ ሲንቀሳቀስ የመንን እንደመሸጋገሪያ በሚጠቀምበት ወቅት በሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ.ም. በየመን ሰንዓ ከተማ በሚገኘው አውሮፕላን ማረፊያ ላይ በሀገሪቱ መንግሥት ትዕዛዝ በፀጥታ ኃይሎች ቁጥጥር ስር መሆኑን ለማወቅ ተችሏል:: ምንም አይነት ምድራዊም ይሁን ሰማያዊ መነሻ ምክንያት ለአቶ አንዳርጋቸው በየመን መንግሥት መታገት እና መታሰር ምክንያት ሊሆን እንደማይችል እንደማይገባም በመግለጽ የየመን መንግሥት የነፃነት ታጋያችንን ባስቸኳይ እንዲለቅ ላለፉት ተከታታይ ቀናት የተደረገው ሁሉን አቀፍ ጥረት ውጤት አላስገኘም:: ከዚህም በመነሳት አቶ አንዳርጋቸው ለዘረኛው እና ከፋፋዩ የወያኔ ቡድን ሊሰጥ ይችላል የሚለው ስጋታችን ቀን በገፋ እና ምላሽ በራቀ ቁጥር እየጨመረ መጥቷል::

በግንቦት 7 ሕዝባዊ ኃይል በኩል የነፃነት ታጋዩ ለወያኔ ተላልፎ መሰጠቱን መቶ በመቶ እስከምናረጋግጥበት ቅጽበት ታጋዩን የማስለቀቅ ጥረቱ መቀጠል እንዳለበት በጽኑ እናምናለን:: አንዳርጋቸውን ማሰር ይቻላል፤ ምናልባትም በዚህ ቅጽበት ተችሏል፤ አንዳርጋቸውን ማሰቃየት ይቻላል፤ ምናልባትም በዚህ ቅጽበት ተችሏል፤ አንዳርጋቸውን መግደል ይቻላል። ሞትን ፈርቶ ወደ ትግል አልገባምና አንዳርጋቸውን በማሰር የአንዳርጋቸውን እንደ እቶን የሚያቃጥል የፍትህ፣ የነፃነት፣ የዴሞክራሲና የእኩልነት መንፈስ ግን ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ከግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የተሰጠ ልዩ መግለጫና … ( ከገጽ 1 የዞረ )

የየመን መንግሥትና ሕዝብ ይህን እንዲያውቁት ማድረግ ወቅቱ የሚጠይቀው የተግባር እንቅስቃሴ አካል ነው።

የመንን በተመለከተ የሚቀጥለው ሳምንት ዘመቻችን ግብ ቁጣችንን የየመን ፕሬዚዳንት እና የየመን መንግሥት ብቻ ሳይሆን የየመን ሕዝብም እንዲያውቅ ማድረግ ነው። የሚከተሉት ተግባራት ለአብነት ያህል ተጠቅሰዋል።

ለየመን ፕሬዚዳንት አዲስ መረር ያለ ደብዳቤ ተጽፎ በፋክስና በኢሜል በየመን መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶችና ኤምባሲዎች አድራሻዎች መላክ። በመልዕክት መጨናነቅ ከሚገባቸው የየመን ተቋማት አንዱ አዲስ አበባ የሚገኘው የየመን ኤምባሲ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ሆናችሁ በዘመቻው የምትሳተፉ ጥንቃቄ እንዳይለያችሁ እናሳስባለን፤ የኢንተርኔትና የፋክስ መልክቶችን ስትልኩ ራስን ለጉዳት በማያጋልጥ መንገድ መደረግ ይኖርበታል።

የየመን ኤምባሲዎችን ሥራ ማወክ በሚችሉ ሰልፎችና ተቃውሞዎች ማጨናነቅ። የፕሬዚዳንቱን ፎቶና የአገሪቱን ባንዲራ ማቃጠል። ይህ በውጭ አገራት ብቻ መደረግ ያለበት ነው።

በውጭ አገራት በየከተሞች ለሚገኙ የየመን ኮሚኒቲዎች ደብዳቤ መፃፍና መንግሥታቸውን እንዲቃወሙ መገፋፋት፤ ይህንን ካላደረጉ ግን ከመንግሥታቸው ጎን ተሰልፈው በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት እንዳወጁ የምንቆጥረው መሆኑን በማያሻማ መንገድ መንገር፤

በየመን አየር መንገድና በማናቸው የየመን የንግድ ድርጅቶችና ቢዝነሶች ላይ እቀባ ማድረግ፤ በቢዝነሶቻቸው ላይ አሉታዊ ቅስቀሳ ማድረግ። ይህ ተግባር በኢትዮጵያም ከኢትዮጵያ ውጭም በሚገኙ ኢትዮጵያዊያን መተግበር የሚኖርበት አቢይ ተግባር ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የየመን ቢዝነሶችን መርጦ ምርቶቻቸው እና አገልግሎቶቻቸው እንዲጠሉ ማድረግ። ከእንግዲህ በየመን ገንዘብ የተሠራ ወይም ከየመን የመጣ ብስኩትም ይሁን ሲጃራ የወገናች ደም የነካው እቃ ነው።

**ብርታኒያን በተመለከተ**

የእንግሊዝ መንግሥት ማድረግ የነበረበትን እና ማድረግ ይችል የነበረውን ሁሉ አድርጓል ብለን አናምንም። እርምጃው ፈጣን አልነበረም፤ አሁንም አይደለም። ስለሆነም እንግሊዝን በተመለከተ የዘመቻችን ግብ የእንግሊዝ መንግሥት ለጉዳዩ ትኩረት በመንፈጉ መክሰስ እና ከአሁን በኋላም ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ እንዲከታተለውና መሪያችን እንዲያስፈታ መወትወት ነው። የሚከተሉት ተግባራት ለአብነት ተዘርዝረዋል።

1. የእንግሊዝ መንግሥትን በህግ መክሰስ (ይህ በንቅናቄው ጽ/ቤት የሚሠራ ሲሆን ዝርዝሩ ወደፊት ይገለፃል)፤
2. ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አዲስ ደብዳቤ ጽፎ በፋክስና በኢሜል ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና ለኤምባሲዎች በብዛት መላክ። አንዱ ትኩረት የሚደረግበት ኤምባሲ አዲስ አበባ የሚገኘው የእንግሊዝ ኤምባሲ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ በዘመቻው የሚሳተፉ ወገኖች አስፈላጊው ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል።
3. በለንደን በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደጃፍ፤ በሌሎች አገሮች ደግሞ በእንግሊዝ ኤምባሲዎች ቁጣ የተቀላቀለበት የተቃውሞ ሰልፎችን ማካሄድ።

**ወያኔን በተመለከተ**

ወያኔን በተመለከተ የሚደረጉ ትግሎች በሙሉ **ወያኔን ከስልጣን ማስወገድን** ያነጣጠሩ መሆን ይኖርባቸዋል። ወያኔም ለመጣል ትልቁን ድርሻ የሚያበረክተው ሕይወታቸውን ለመስጠት የቆረጡ፡ ከቁም ውርደትና ባርነት ለነጻነትና ለፍትህ ከወያኔ ጋር ጉረሮ ለጉረሮ እየተናነቁ እየጣሉ ለመውደቅ ፤ መስዋእት ለመሆን በወሰኑ ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችንና የህዝብ ሃይሎች የሚያደርጉት ተግባራዊ እንቅስቅሴ ነው ፤ እንቅላቀላቸው።

በተለያዩ ምክንያቶች ወሳኙን ትግል መቀላቀል የማይችሉ ወገኖቻችን በያሉበት ሆነው ከወያኔ የስለላ መረብ ተጠነቅቀው ራሳቸውን በቡድን ያደራጁ፤ ይህንኑ የሚያግዙ ተግባራት ለመፈጸም ራሳቸውን ያዘጋጁ። እነዚህ ተግባራት ወያኔን በገቡበት እየገቡ በማሳፈር፤ እረፍት በመንሳት፤ የፈፀሟቸውን ወንጀሎች በአደባባይ በመናገር እንዲሸማቀቁ በማድረግ፤ ማንነታቸው ለሸሪኮቻቸው ወይም ለሥራ ባልደረቦቻቸው በመንገር ወዳጅ በማሳጣት፣ ንግዶቻቸውን ኩባንያዎቻቸው እንዲከስሩ በማድረግ የፋናንስ አቅማቸው በማዳከም ረገድ የሚኖራቸው አስተዋጽኦ ቀላል እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል። ከዚህ አኳያ ሊደረጉ ከሚገቡ ተግባራት የሚከተሉት በምሳሌነት ተዘርዝረዋል።

1. በምዕራቡ ዓለም በተለያዩ ሽፋኖች ተሰግስገው ያሉት እና የሚመላለሱ ወንጀለኞች የወያኔ ሹማምንትና ደጋፊዎችን ለፍርድ ለማቅረብ መደራጀትና እንደየሀገሩ ሁኔታ አግባብ ያላቸውን የህግ መሳሪያዎች መጠቀም፤
2. በመላው ዓለም የወያኔ ኤምባሲዎችና የኮንሱላር ጽ/ቤቶች ሥራ መሥራት የማይችሉበት ሁኔታ መፍጠር፤
3. በመላው ዓለም የወያኔ አባላትና ደጋፊዎችን ከያሉበት (ከሰፈር፣ በዩኒቨርስቲዎች፣ በንግድ የተሰማሩ ..) በማደን ማስነወር፣ ማግለል፣ ማዋረድ፤ ከእነሱ ጋር አንዳችም የንግድም፡ የሥራ ፤ የማኅበራዊ ትብብርና ግንኙነት አለማድረግ፤ ፊት መንሳት፤ በሥራዎቻቸው ላይ አሉታዊ ቅስቀሳዎችን ማካሄድ። የወያኔ አባላትንና ደጋፊዎችን በሁሉም ዓይነት ግንኙት ማግለል፡ አለመተባበር በኢትዮጵያም ውስጥ በስፋት በሥራ ላይ መዋል ይኖርበታል።
4. በማናቸውም የዓለም ክፍል ለሥራ ወይም ለሽርሽር የሚዘዋወሩ ከፍተኛ የወያኔ ሲቪል፣ የወታደራዊና የደህነት ባለሥልጣኖችና የጦር መኮንኖችን እየተከታተሉ ማሸማቀቅ፣ ማስነወር፣ መውጫ መግቢያ ማሳጣት፤ በየትኛውም የዓለም ክፍል ተቀባይነት እንደሌላቸው በሕዝብ ላይ ለፈጸሙት ወንጀሎች ሁሉ የሕዝብ ቁጣ ዒላማ እንዲሆኑ እንደልባቸው መፏለል እንዳይችሉ ማድረግ። በኢትዮጵያ ውስጥ ሕዝብ ራሱ በቡድን አደራጅቶ ለወያኔ ታጣቂዎች ጥቃት ሳያጋልጡ አድብቶና አስልቶ ተመሳሳይ ድርጊቶች መፈፀም
5. የኢትዮጵያ አየር መንገድን ጨምሮ በወያኔ አገዛዝ የሚመሩ እንዲሁም በወያኔ ኤፈርት ስር ያሉ ኩባንያዎች፤ቢዝነሶች ላይ እቀባ ማድረግ፤ የሸቀጥና የአገልግሎታቸው ተጠቃሚ አለመሆን፤ በእነሱ ላይ አሉታዊ ቅስቀሳ ማድረግ፤ በልዩ ልዩ መንገዶች ሥራቸውን ማጨናገፍ ማደናቀፍ፤ አሻጥሮችን በተደራጀ መልክ፣ በጥናትና በብልሃት ተግባራዊ ማድረግ። ይህ በኢትዮጵያም በመላው ዓለም በሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል።
6. በዌስተር ዩኒየን፣ በመኒ ግራም እንዲሁም በአሜሪካ፣ በአውሮፓ፤ በመካከለኛው ምሥራቅ በወያኔ ደጋፊዎች በሚመሩ ልዩ ልዩ የገንዘብ ላኪ ድርጅቶች በኩል ገንዘብ ወደ ኢትዮጵያ አለመላክ፤ በየአካባቢው አማራጭ የገንዘብ መላኪያ መንገዶችን መፈለግ፤ እነዚህ በሌሉባቸው አካባቢዎች የፈጠራ ችሎታን በመጠቀም ገንዘብ ለዘመድ አዝማድ በወያኔ በኩል ሳይላክ የሚደርስበትን ሁኔታ መፍጠር፤ የወያኔን የፋሽስታዊ አገዛዝ አንዱና ዋነኛ ምሰሶ የሆነውን የውጭ ምንዛሪ የማድረቂያ ዘዴዎችን ሁሉ በመፈለግ ተግባራዊ በማድረግ የወያኔን በዘረኝነትና በዘረፋ የተገነባ የገንዘብና የኢኮኖሚ አቅም ማዳከም፤ መቦርቦር፤ መናድ።
7. ከወያኔ ጋር የሚሠሩ የውጭ አገር ድርጅቶች ከወያኔ ጋር ያ ያላቸውን ሽርክና እንዲያቋርጡ መወትወት፤ አልሰማ ካሉ በቢዝነሳቸው ላይ አሉታዊ ቅስቀሳ ማካሄድ። (የእነዚህን ዝርዝሮች በተከታታይ ይገልጻሉ)
8. የምዕራብ አገራት ዩኒቨርስቲዎች ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸውን ግኑኝነት እንዲመረምሩ ማሳሰብ። በተለይ ደግሞ ሳያስተምሩ ለወያኔ ሹማምንቶች ዲግሪ የሚያድሉ ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆችን ማስጠንቀቅ፤ ተግባሮቻቸውን ለተማሪዎቻቸው ጭምር መንገር (ለምሳሌ University of Greenwich ከ International Leadership Institute ጋር ያለውን ግኑኝነት እንዲሰርዝ፣ እስከዛሬ የሰጣቸውንም የማስትሬት ዲግሪዎች እንዲመረመር የሚጠይቅ ደብዳቤ ጽፎ በብዛት በፋክስ መላክ፤ ተመሳሳይ ደብዳቤ Open University እና ከወያኔ ጋር ተሻርከው ለሚሠሩ ዩኒቨርስቲና ኮሌጆች መላክ)
9. ይህ ዘመቻ ለጊዜው በወያኔ ላይ ያነጣጠረ ቢሆንም፣ የሕዝቡን የነፃነትና የፍትህ ጥረት የሚያደናቅፉ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ አገር ዜጎች በሆኑ ቱጃሮችና ከወያኔ ጋር የተያያዙ የንግድ ቤቶችና ኩባንያዎች የዘመቻው ዒላማ ሊሆኑ ይችላሉ። (ዝርዝራቸውን በተከታታይ እናወጣለን)

በመጨረሻም የወጣቱ የማያልቅ የፈጠራ ችሎታ ከላይ በዝርዝሩ ውስጥ ያልተካተቱ ሆኖም ግን ውጤታማ የሆኑ የተቃውሞ መግለጫ ዘዴዎች ያፈልቃል ብለን እናምናለን። ስለሆነም ዘመቻውን በየአካባቢው በሚገኝ ሀሳብና ፈጠራ ማዳበር ይቻላል። ይህ ዘመቻ ወያኔ ከስልጣን እስኪባረር ድረስ በየጊዜ እየከረረ መሄድ እንዳለበት ታሳቢ አድርጎ መነሳት ይኖርበታል። ስለሆነም በየጊዜው አዳዲስ ነጥቦችን ተግባራዊ የትግል ስልቶችን እንጨምራለን።

ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በመላው ዓለም የምትገኙ ኢትዮጵያዊያን ዜጎች ሁሉ፣ ለሁሉም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሁሉ በኅብረት በጋራ ሆነን፣ ተከሻ ገጥመን ለተግባራዊ ትግል በቁርጠኝነት እንድንነሳ ጥሪያችንን እናቀርባለን ።

ይህ ዘመቻ ወያኔን ከስልጣን ለማባረር ምድር ላይ ከምናደርገው የመረረ ትግል ጋር ሲቀናጅ የሚፈለገውን ውጤት ስለሚያስገኝ ለነፃነቱ ግድ ያለው ዜጋ ሁሉ በሙሉ ኃይሉና አቅሙ ተሳትፎ እንዲያደርግ ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ አገራዊ ጥሪ ያቀርባል።
በመስዋዕትነት ድልን እንቀዳጃለን !!!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!!

**በመስዋዕትነት ድልን እንቀዳጃለን !!!**
**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!!**

# ጥቂት ነጥቦች በፍትህ ጉዳይ ላይ

(ታደሰ ብሩ )

## 1. መግቢያ

ህወሓት በሥልጣን ላይ በከረመ መጠን የኢትዮጵያ ሕዝብ በፍትህ እጦት የሚደርስበት መከራ እየጨመረና እየመረረ በመምጣቱ "ፍትህ አጣን፤ የፍትህ ያለህ" የሚሉ እሮሮዎች ከቀድሞው በበለጠ መልኩ እየጎሉ መጥተዋል። በከተማውም በገጠሩም፣ ከእድሜ ባለፀጋውም ከወጣቱም፣ ከወንዱም ከሴቱ፣ ከክርስቲያኑም ከሙስሊሙም ወገኖቻችን የሚሰማው ጩከት "የፍትህ ያለህ" የሚል ነው። የፍትህ እጦት ነው ወገኖቻችንን በገዛ አገራቸው ተፈናቃይ ያደረጋቸው፤ የፍትህ እጦት ነው ገበሬዎች ማሳቸው ለባዕዳን ሲሰጥ አንጀታቸው እያረረ ዝም እንዲሉ የሚያደርጋቸው፤ የፍትህ እጦት ነው ነጋዴዎች ሱቆቻቸው በእሳት ሲጋዩ "ጉዳዩ ይጣራልን" ማለት እንኳን ያላስቻላቸው፤ የፍትህ እጦት ነው የእምነት ነፃነታችንን እንኳን ማስከበር ያላስቻለን።

ፍትህ ሰዎች በግልም በቡድንም ተሳስበው እና ተጋግዘው እንዲኖሩ የሚያደርግ የበጎ ሥነ-ምግባር መርሆች ስብስብ ነው። ፍትህ ነው ማኅበረ-ሰብን ከማኅበረ-አራዊት የሚለየው። ማኅበራዊ ኑሯቸውን በሥርዓት አደራጅተው የሚኖሩ እንስሳት መኖራቸው ቢታወቅም (ለምሳሌ የጉንዳን ሠራዊት፤ የንብ መንጋ) በእውቅ (Consciously) የተገነባ የፍትህ ሥርዓት ያለው የሰው ልጅ ብቻ ነው። ፍትህ ሰውኛ እሴት ነው።

ምንም ዓይነት ፍትህ የሌለበት ማኅበረሰብን ለማሰብ ብንሞክር በአዕምሮዓችን ሊመጣልን የሚችለው እያንዳንዱ ግለሰብ፣ ከፍ ካለ ቤተሰብ፤ ከዚህ በላይ ከፍ ካለ ደግሞ የተዛመዱ ቤተሰቦች የፈጠሩት ስብስብ ነው። እያንዳንዱ ግለሰብ ወይም በዝምድና የተሳሰረ ስብስብ የገዛ ራሱን ወይም ቡድኑን ለማኖርና ከጥቃት ለማዳን የሚጥርበት ሥርዓት እናገኛለን። በዚህ ሥርዓት ውስጥ "የሥጋ" ዝምድና (ለምሳሌ እናትና ልጅ) ብቸኛው ማስተሳሠሪያ ይሆናል። በሌላ አነጋገር ዘር ብቸኛ የስብስቡ ማስተሳሠሪያ ይሆናል። በማኅበረ-እንስሳት ውስጥ መንጋን የሚያስተሳስረው በዘር መነሻነት የተፈጠረ አብሮ ውሎ ማደር ነው። ፍትህ በሌለበት ማኅበረሰብም ውስጥ የሚዛመዱ ቤተሰቦች ራሳቸው በተለያየ ስያሜ ወደሚጠሩ ስብስቦች ማደግ ይችላሉ። ትልቅም ይሁኑ ትንሽ፣ ስብስቦቹን የሚያገናኛቸው ዝርያቸው ነው። በማኅበረ-እንስሳት ውስጥ በመንጋዎች መካከል የማያቋርጥ ትንንቅ ይኖራል። በማኅበረ-እንስሳት ደካማው ብቻ ሳይሆን ጠንካራውም ቢሆን ሕይወቱን በሰቀቀን ማሳለፉ የግድ ነው። ጠንካራው መንጋ ከሱ የባሰ ጠንካራ መንጋ እንዳይመጣበት እንደሰጋ ይኖራል። ፍትህ የሌለበት ማኅበረሰብም እንደዚያው ነው። ፍትህ በሌለበት፣ ሰዎች በዘር መደራጀታቸው ተፈጥሮዓዊ የመሆኑን ያህል እርስ በርሳቸው መጣላታቸውም እንደዝያው የማይቀር ተፈጥሮዊ ነው። በቡድኖች መካከል ያለው ጦርነት በአንዱ ቡድን ጊዜዓዊ አሸናፊነት ጋብ ሲል በቡድኑ ውስጥ ባሉ ቤተሰቦች መካከል ጦርነት ይነሳል፤ ያ ጋብ ሲል ደግሞ በእያንዳንዱ ግለሰብ መካከል ይጀመራል። ሲከፋ ወገንና ጠላት ያልለየ ሁሉም ከሁሉም ጋር (all against all) ጦርነት ውስጥ ይገባል። ይህ ዓይነቱ ሁኔታ ነው ህገ-አራዊት የሚባለው። ፍትህ በሌለበት የሰው ልጆች ሕይወት ወደ ህገ-አራዊት ያሽቆለቁላል።

ወያኔ አገራችንን እንዲህ ወደ አለ አስቀያሚና አስፈሪ ሁኔታ እየገፋት ነው። ፍትህ ድራሿ ጠፍቶ፣ ዘር ብቻውን የኑሮ መሠረት ሲሆን የቁልቁለት ጉዟችን የሚያደርሰን ወደ ህገ-አራዊት መሆኑ የማይቀር ነው።

## 2. ህግ፣ ፍትህ እና የህግ የበላይነት

ህግ እና ፍትህ በጥብቅ የተቆራኙ ቢሆንም የተለያዩ ጽንሰ-ሀሳቦች ናቸው። ህግ "ይህንን አድርግ፤ ያንን አታድርግ" የሚል ድንጋጌ ነው። አቅም ያለው ሁሉ የፈለገውን ህግ አውጥቶ ሊያስፈጽም ይችላል። ፍትህ፣ ሰዎች ተሳስበው እና ተጋግዘው እንዲኖሩ የሚያደርግ፤ አድዎንና ጥቃትን የሚከላከል፤ በዳይን የሚቀጣ፣ ተጠቂን የሚክስ በጎነት ነው። ፍትህ የማኅበራዊ ተቋማት ቀዳሚ በጎ ውጤት ነው። ህግ መሣሪያ ሲሆን ፍትህ ህጉ በተግባር ላይ ሲውል የሚገኘው ውጤት ነው። ጥሩ ህግ በሥራ ላይ ከዋለ ፍትህን ያስገኛል። ጥሩ ህግ ኖሮ ሥራ ላይ ካልዋለ ህጉ መኖሩ ብቻውን ፍትህን አያስገኝም። መጥፎ ህግ ደግሞ ፍትህን ያጓድላል፤ ኢፍትሃዊነትን ያነግሳል። "የህግ የበላይነት" ሲባል በሁሉም ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ህግ አለ ማለት ነው።

የህግ የበላይነት እንዲከበር ቢያንስ ሁለት ነገሮች መሟላት ይኖርባቸዋል።

**2.1.** ህግ፣ ፍትሃዊ ይሁንም አይሁን፣ ያለ አድልዎ በሥራ ላይ መዋል አለበት መጥፎም ይሁን ጥሩ፣ አንድ ህግ በሁሉም ላይ እኩል ሥራ ላይ ከዋለ የህግ የበላይነትን አንድ መሠረታዊ መሥፈርት አሟላ ማለት ይቻላል። በተለይም ህግ አስፈፃሚው በህጎቹ ራሱ የሚገዛባቸው መሆን አለመሆኑ ቁልፍ ጉዳይ ነው። ህግ አውጭው የሚያወጣቸውን ህጎች ህግ አስፈፃሚው ሲፈልግ በሥራ ላይ የሚያውላቸው፣ ሳይፈልግ ደግሞ የሚተዋቸው ከሆነ፣ የህጎቹ መኖር ለህግ የበላይነት መከበር የሚሰጠው ፋይዳ የለም።

በሀገራችን ወያኔ የሚያወጣቸው ከልካይ ህጎች ተቀናቃኞቹን እንጂ ራሱን ወያኔን አይከለክሉትም። ለምሳሌ በፀረ-ሽብር ህጉ፣ የወያኔ አሻንጉሊት ፓርላማ በሽብርተኝነት ከፈረጃቸው ድርጅቶች ጋር መነጋገር ያስቀጣል። ይህ ክልከላ ግን በራሱ በወያኔ ላይ አይሠራም፤ ከአብነግ ጋር ይፋ ለሆነ ድርድር ላይ መቀመጡ በራሱ ሚዲያ በይፋ ገልጿል። "ግንቦት 7 ከኤርትራ መንግሥት ጋር ተባብሮ ይሠራል" ሲል በከሀዲነት ይወነጅላል፤ ወያኔ እራሱ ግን ከሰባ ጊዜ በላይ ከኤርትራ ጋር አብሮ ለመሥራት ሙከራ አድርጎ እንዳልተሳካለት በመግለጽ ያማርራል።

ወያኔ የሚያወጣቸው ህጎች ፍትሃዊነት የጎደላቸው ቢሆንም እንኳን በትክክል ሥራ ላይ ውለው ቢሆን ኖሮ የተሻለ ነበር። ወ/ት ርዕዮተ ዓለሙ ላይ በመጀመሪያ 14 ዓመት ከዚያ ደግሞ በይግባኝ 5 ዓመት የተፈረደባት የፀረ-ሽብር ህጉ መጥፎ ስለሆነ ብቻ አይደለም። ዳኝነትና ዳኛ ቢኖር ኖሮ በዚሁ ህግ ተከራክራ ነፃ መውጣት ትችል ነበር። ዳኝነት ኖሮ ቢሆን ኖሮ እስክንድር ነጋ በተከሰበት ኢፍትሃዊ ህግም ቢሆን ተከራክሮ ነፃ ይወጣ ነበር። የአንዱዓለም፣ የሙስሊም ማኅበረሰብ መሪዎች እና ሌሎች በርካታ ወገኖቻችን ጉዳይም እንደዚሁ ነው፤ ዳኝነት ቢኖር ኖሮ በተከሰሱበት ህግ ተከራክረው ነፃ መውጣት ይችሉ ነበር። ዳኝነት ኖሮ ቢሆን ኖሮ ብዙዎቹ ተከሳሾች መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነፃ ይሰናበቱ ነበር።

ዛሬ አገራችን ውስጥ ያለው የህግ ችግር የመጥፎ (የኢፍትሃዊ) ህጎች መብዛት ብቻ አይደለም። ችግራችን ከዚያም ያልፋል። ባጠቃላይ የሚሠራ ህግ የለም፤ ዳኝነት የለም። ህገ-አልባነት ህግ ሆኗል።

**2.2. የህጎች ፍትሃዊ መሆን አስፈላጊነት**

ህግ ሁሉ ግን ወደ ፍትህ አያደርስም። ፍትህን የሚያሰፍኑ ህጎች አሉ፤ ኢፍትሃዊነትን የሚያሰፍኑ ህጎችም ሊኖሩ ይችላሉ። የወንድና ሴት መሳሳም የሚያስቀጣበት አገር አለ። እንደኛ አገር ደግሞ መንግሥት ያልወደደውን ጋዜጣ ማንበብ የሚያስቀጣበት አገር አለ። የህግና የፍትህ ግኑኝነት ውስብስብ ነው። ለምሳሌ፣ "ሰዎች ሁሉ እኩል መስተናገድ አለባቸው" የሚል ህግ ቢወጣ በግልቡ ሲታይ ችግር ያለው ባይመስልም በሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ግን ፍትሃዊ ላይሆን ይችላል። አንድ የጤና ጣቢያ ለአንድ ጤነኛ ባለጉዳይ እና የአካል ጉዳት ላለበት ሌላ ባለጉዳይ እኩል መስተንግዶ መስጠት አለብኝ ቢል ኢፍትሃዊ ነው። ከሚሰጠው አገልግሎት እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ የአካል ጉዳተኛው የተለየ መስተንግዶ ሊሰጠው ይገባል። ከላይ በምሳሌነት የተጠቀሰው ዓይነት በደምሳሳው ሲታይ ችግር ያለበት የማይመስል ቀና ህግ እንኳን በሥራ ላይ በሚውልበት በፍትህ ሚዛን መታየት ይኖርበታል።

ህግ ተብለው በሥራ የሚውሉ ድንጋጌዎች ገና ከመነሻው በማያሻማ ሁኔታ ከፍትህ ጋር የተጣሉ ሲሆኑ ምን ይደረጋል? ለምሳሌ፣ መነጋገርንና ማሰብን የሚከለክል ህግን እንዴት መቀበል ይቻላል? ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግን የሚከለክል ህግን እንዴት መቀበል ይቻላል? መደራጀትን የሚከለክል ህግ እንደምን መቀበል ይቻላል? ለፍትህ ግድ ያለው ሰው ወይም ቡድን እንዲህ ዓይነት ህጎችን በማክበር ሳይሆን በመጣስ ነው ለፍትህ ዘብ መቆም የሚችለው። በህግ የበላይነት ሰበብ ለኢፍትሃዊ ህጎች መገዛት ከተጠያቂነት የማያድነውም ከህጎች ሁሉ በላይ የሆነው የፍትህ ስሜት በውስጣችን ሊኖር ስለሚገባው ነው። ዛሬ በወገኖቻችን ላይ ሰቆቃ እየፈፀሙ (ቶርቸር እያደረጉ) ያሉ አረመኔዎች ዛሬ ያለው ህግ ይህን እንዲፈጽሙ ቢያዛቸው እንኳ ነገ ሲጠየቁ "እኔ ህጉ ያዘዘኝን የፈፀምኩት፤ የሥራ ግዴታዬን ነው የተወጣሁት" ማለት የማያድናቸው ኢፍትሃዊ ትዕዛዝን፣ ደንብንም ሆና አዋጅን የመቃወሚያ ህሊና የተሰጣቸው በመሆኑ ነው።

ሰው ሆነን ተፈጥረን በሰዎች ማኅበር ውስጥ በማደጋችን ብቻ የተወሰነ የፍትህ ስሜት በውስጣችን አለ። በዚህ የፍትህ ስሜት (በተለምዶ አነጋገር በህሊና ዳኝነት) የሚገዛ ማንኛውም ሰው በራሱ ላይ እንዲደርስ የማይፈልገውን ነገር በሌሎች ላይ አያደርስም፤ ሌሎች በሌሎች ላይ ጥቃት ሲያደርሱም አይቶ ዝም አይልም። ህሊናችን ኢፍትሃዊ ህጎችን ይፀየፋል።

## 3. ኢትዮጵያ፣ ህግና ፍትህ

ኢትዮጵያ አገራችን የብዙ ወለፈንዲዎች (Paradoxes) አገር ናት። ከእነዚህ ወለፈንዲዎችም አንዱ ፍትህና ህግ በኢትዮጵያ ያላቸው ቦታ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድ በኩል ህግ አክባሪ ነው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ፍትህ የተነፈገ ሕዝብ ነው። እንዴት ፍትህ የተነፈገ ሕዝብ ህግ አክባሪ ይሆናል? ይህ ለመረዳት የሚቸግር ወለፈንዲ ነው።

ለኢትዮጵያዊያን "በህግ አምላክ" ትልቅ ትርጉም ያለው ሀረግ ነው። ድሮ (ከወያኔ በፊት) ተበዳይ በዳያን አግኝቶ "በህግ አምላክ ቁም ብዬሃለሁ" ካለው ፓሊስ እንኳን ባይኖር ምስክር ወይም ገላጋይ እስኪመጣ ድረስ "ቁም" የተባለው ሰው ባለበት ይቆም ነበር። "የህግ አምላክን" ማክበር አምላክን ከማክበር ጋር እኩል ነበር። "የህግ አምላክ" መኖሩ ተገዢዎች በህጉ ተፈፃሚነት ላይ እምነት እንዲኖራቸው አድርጓል። ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## የመን አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ለወያኔ ፋሽስቶች አሳልፋ መስጠቷን በማስመልከት … ( ከገጽ 1 የዞረ )

የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ህገ ወጥ እገታ ከተሰማ ዕለት ጀምሮ የፖለቲካ ልዩነት አጥር ሆኖ ሳይከልላችሁ ከጎናችን ለቆማችሁ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማኅበራትና ዜጎች ሁሉ ምሥጋናችንን እናቀርባለን። በወገናዊ ተግባራችሁ ልባችን ተነክቷል። ከዚህ በላይ ደግሞ ለቀጣዩ ወሳኝ ፍልሚያም እንደምንቆም እና የወያኔን እድሜ እንደምናሳጥር እምነታችን አጠንክሮልናል።

ከዛሬ ጀምሮ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ አንዳርጋቸው ጽጌን ሆኗል። ዛሬ ዘጠና ሚሊዮን አንዳርጋቸው ጽጌዎች በአንድነት ተነስተዋል። በአንድ አንዳርጋቸው ጽጌ ላይ የደረሰው ጥቃት ሰበብ ሆኖ የተቀሰቀሰው የሕዝብ ቁጣ የወያኔ ፋሽስቶችን ይጠራርጋል። በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ላይ ለደረሰውና ለሚደርሰው ጥቃት እያንዳንዱ የወያኔ ሹም በግል ዋጋ ይከፍላል። ከእንግዲህ በምሬት የተነሳሳው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሚወስደው እርምጃ ተጠያቂው ራሱ ወያኔ መሆኑን እውን ሆኗል። በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ እስር የከተት አዋጅ ታውጇል። ለፍትህ፣ ለነፃነት፣ ለሀገር፣ ለእኩልነት ግድ ያለህ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ተነስ!!!

**በመስዋዕትነት ድልን እንቀዳጃለን።**
**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## አንዳርጋቸው የማይጨበጥ ጽኑ መንፈስ እንጂ አንድ ግለሰብ

… ( ከገጽ 1 የዞረ )

ለሴኮንዶች እንኳን ማሰር አይቻልም። አንዳርጋቸውን በማሰቃየት ያን ዘመን ተሻጋሪ የሆነ የትውልዱን መንፈስ የሚገዛ የሁላችንም የምትሆን የጋራ ኢትዮጵያን የመፍጠር ንጹህ ራዕዩን ግን ፈጽሞ ማቁሰል አይቻልም!!! አንዳርጋቸውን በመግደል ዕንቁ ዓላማውን መግደል ከቶ አይቻልም፣ የታሪክ መዘግብት ገጾች ለዚህ ሃቅ በሚመሰክሩ እውነታዎች የተሞላ ነውና።

አንዳርጋቸውን በመግደል "ከአባቶቹ የማይበልጥ ትውልድ እንዳልተፈጠረ ይቆጠራል፣ ልጅ አባቱን ሩጦ መቅደም አለበት፣ ስለዚህ እናንተ ወጣቶች እኛን ሩጡ እና ብለጡ ቅደሙን፣ ቀናዎች ሁኑ፣ ርስ በርስ ተዋደዱ፣ ያለፉት ትውልዶች የሰሩትን ስህተት ላለመድገም ታሪክን ከስሩ ተረዱ፣ ያለማወቅ ጠንቅ ከሚያመጣው ጥፋት ለመዳን ሁሌም ለእውቀት ጉጉዎች ሁኑ። ለማወቅ ጣሩ፣ የማይቀረው ሞታችሁ ለፍትህ፣ ለዴሞክራሲ እና ለነፃ ኢትዮጵያ ይሁን" እያለ ላለፉት በርካታ አመታት ያስተማራቸው እና የኮተኮታቸው የነፃነት ታጋይ አርበኛ ወጣቶችን እና እሳት መንፈሳቸውን መግደል አይቻልም።

ታሪካዊ ስህተት በመሥራት በአዲሱ ትውልድ ልብ ውስጥ የበቀለ እና የቂም ጓዝ ለማስቀመጥ እየተንደረደረ ያለው የየመን መንግሥትም ሆነ ወያኔ ሊያውቁት የሚገባው ተፈጥሯዊ ሃቅ ይህ ነው። አንዳርጋቸውን በአንድ ካቴና በማሰር፤ በአንድ ክፍል ውስጥ በመዝጋት ወይም በአንድ ጥይት በመግደል "መገላገል" የሚቻል አንድ ግለሰብ አይደለም። አንዳርጋቸው ለሽህ ካቴናዎች የማይታጠፉ እጆች፣ ለሽህ ማጎሪያዎች የገዘፈ ገላ፣ ለሽህ ጥይቶች የሰፋ እና ሽህ ጥይቶችን የሚተፋ ግንባር እና ደረት ያለው ብርቱ ታጋይ ነው። አንዳርጋቸው አንድ ግለሰብ አይደለም፤ የማይጨበጥ ጽኑ መንፈስ እንጅ!!!

አንዳርጋቸው ለአርባ አመታት በሚጠጋ የፖለቲካ ሕይወቱ ሁሉ በረሃ የሚወረወረው አፈር ላይ የሚንከባለለው፤ በእሱ እድሜ በማይታሰብ ሁኔታ እንኳን የበረሃ ሃሩር፣ ጥም እና ረሃብ የሚያንገላታው ነገ ኢትዮጵያን በፕሬዝዳንትነት ወይ ደግሞ በጠቅላይ ሚኒስቴርነት ለመምራት ካለው ሰዋዊ ፍላጎት አይደለም። የሱ ምኞት የሁላችንም የሆነች ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ማየት ነው!!! ይህን በተለይ የግንቦት ሕዝባዊ ኃይል አመራሮች እና መላው አባላት ጠንቅቀን እናውቃለን። አንዳርጋቸው ሁሌ ለሚያልማት ንጽህት ኢትዮጵያ መሥራት የነበረበትን ፈታኝ እና ታሪካዊ ሥራዎች ቀድሞ አከናውኗቸዋል። ላለፉት 6 እና 7 ዓመታት ከጥልቅ የፖለቲካ ተሞክሮው እየቀዳ ለወጣት ኢትዮጵያውያን በየበረሃው እየዞረ አስተምሯል። እያማጠ አደራ ብሏል። እያለቀሰ ምኞቱን፣ ፍላጎቱን እና ራዕዩን ከውስጡ አውጥቶ መዳፋ ላይ በማስቀመጥ ልቡን ለታዳጊዎች አሳይቷል። ንጹህ ዓላማው ሽህ ባለ ራዕዮችን ፈጥሯል የተግባር ሰዎችን አምርቷል። የግንቦት 7 ሕዝባዊ ኃይል አንዳርጋቸው እንደመጥምቁ ዮሃንስ በበረሃ እየዞረ ሲያስተምር እና ሲሰብክ ከፈጠረው ንጹህ የኢትዮጵያዊነት መንፈስ ላይ የበቀለ ኃይል ነው።

ትናንት አብሮ ውሎ ዛሬ በድንገት መተጣጣት የትግል አንዱ ባህሪው ነውና ዛሬ አንዳርጋቸው በአካል አብሮን ላይኖር ይችላል። ነፍሳችን ውስጥ ያሰረፀው ዘላለማዊ መንፈስ ግን እስከመጨረሻ ህቅታችን ድረስ አብሮን ይዘልቃል። አንዳርጋቸውን በማስቆም ትግሉን አቆማለሁ ብሎ የሚያስብ ካለ ዓለምን እና ሁኔታዎችን መገንዘብ የማይችል ከራሱ የተጣላ የወያኔ አይነት ቂል ብቻ ነው። አንዳርጋቸውን በማስቆም ትግሉን ማስቆም አይቻልም። መንፈስን ማስቆም ከቶ ማን ይቻለዋል?? አንዳርጋቸው እኮ መንፈስ ነው። ሁሉም ቦታ፣ ሁሉም ጫፍ፣ሁሉም ልብ ውስጥ የሚገኝ እና የሚንሳፈፍ መንፈስ።

የየመን መንግሥት የፈጸመው ድርጊት እጅግ ስህተት መሆኑን ዘግይቶም ቢሆን ተረድቶ የነፃነት ታጋዮችንን ባስቸኳይ ይለቀው ዘንድ አሁንም ደጋግመን እንጠይቃለን። ይህ ሳይሆ ን ቀርቶ ታጋዮችን ወያኔ እጅ ውስጥ ከገባ ግን የትውልዱ የበቀል ሰይፍ ከዛሬ ጀምሮ ከሰገባው መውጣቱን እንዲያውቁት እንፈልጋለን። ወያኔም ይህ የቂል ድርጊት የነፃነት ታጋዮችን የበለጠ ቁጭት እና የበቀል እርምጃዎች ውስጥ የሚከት መሆኑን አብሮ ሊገነዘበው ይገባል። ለዚህ ቃላችን ታሪክ ምስክር ይሁንብን።

**ድል ለ ኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## ጥቂት ነጥቦች በፍትህ ጉዳይ ላይ

… ( ከገጽ 3 የዞረ )

ገዢዎችም ቢሆኑ ለዳኝነት ክብር እንዲሰጡ "የህግ አምላክ" በተወሰነ መጠንም ቢሆን አገልግሏል። ከፍትህ አንፃር የቀደሙት ሥርዓቶች ብዙ ጉድለቶች የነበሩባቸው ቢሆንም ችሎትን እንደ አሁን መዘባበቻ ያላደረጉበት አንዱ ምክንያት ፍትህን ከመለኮታዊ ሥልጣን ጋር ማያያዛቸው ነው። ይህ እውነታ የኢትዮጵያ ሕዝብ በፍትህ ሥርዓቱ ላይ ከፍተኛ እምነት እንዲያድርበት አድርጓል። አንድ ባለጉዳይ በአንድ ዳኛ ቢፈረድበት "የህግ አምላክ" ስላለ በሚቀጥለው እርከን ላይ ያለው ዳኛ ዘንድ ፍትህን አገኛለሁ በሚል ለአቤቱታ ይጓዛል፤ እዚያም ባይሳካለት ወደሚቀጥለው እርከን አቤት ይላል። እንዲህ እያለ አንዳንዱ እንጉሡ ችሎት ዘንድ ይቀርባል። የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲህ ፍትህ እየተነፈገውም "በህግ አምላክ" ላይ ተስፋ የማይቆርጥ ህገ አክባሪ ሕዝብ ነው። የኢትዮጵያን ሕዝብ ህግ አክባሪነት በችሎቶች ደጃፎች ብቻ ሳይሆን በዘወትር ሕይወቱም የሚታይ ነው። በከተሞች ውስጥ የወርቅ ቤቶችን ግድዳዎች ተደግፈው የሚያድሩ ድሆች ያሉት ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ሳይሆን አይቀርም። ጠመንጃ ይዞ "አገሬ መግቢያ መሳፈሪያ ሙሉልኝ" ወይም "ራበኝ፣ ለምሳ ተዘከሩኝ" የሚል ወታደር የነበረው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። ይህ ሁሉ መልካም ባህል አሁን በዘመነ ወያኔ በዓይኖቻችን ሥር እየተንኮታኮተ ነው። ይህ በቀላሉ የማይገነባ ክቡር ባህል እያጣን ነው።

አሳዛኙ ነገር በዚህ ህግ አክባሪ ሕዝብ ጫንቃ ላይ የተጫኑ ገዢዎች የሕዝቡን ህግ አክባሪነት በሚመጥን መጠን ህግን አክብረው የሚያስከብሩ አለመሆናቸው ነው። በህግ አጠባበቅ ረገድ ኢትዮጵያ እየተጓዘችበት ያለው የቁልቁለት ጉዞ አስፈሪ ነው። ኢትዮጵያ ከአንድ ገገር መዳፍ ወደ ሌላው በተወረወረች ቁጥር ፍትህ ከቀድሞው በባሰ እየተረገጠች መጥታለች። የቅርቡን ዓመታት እንኳን በምሳሌነት ብንጠቅስ የአጼ ኃይለሥላሴ አገዛዝ ኢፍትሃዊነት ያስመረራቸው ወገኖች ሥርዓቱን ታገሉት፤ በትግሉ አሸንፎ የወጣው ግን ከቀድሞው የባሰው ደርግ ሆነ። የደርግ ሥርዓት ያስመረራቸው ታገሉት፤ በትግሉ አሸንፎ የወጣው ግን ከደርግ የባሰው ወያኔ ሆነ። ይህ የቁልቁለት ጉዞ ካልተሰበረ አደጋው በዚሁ ዓይነት ሊቀጥል ይችላል።

ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ የፍትህ እሳቤያችን ራሱ እያሽቆለቆለ መምጣቱ ነው። ቀድሞ፣ ከላይ እንደተገለፀው፣ ፍትህ መለኮታዊ ፀጋ ተደርጋ ትወሰድ ነበር፤ መቀመጫዋም ከአማልክት ጎን ነበር። "በህግ አምላክ" ሲባልም የአማልክት መቀመጫ ነው ተብሎ ወደሚታሰበው ሰማይ እየታየ ነበር። ከማርክሳዊ ሌሊናዊ ርዕዮተዓለም መምጣት ጋር ፍትህ ከሰማየ ሰማያት ወርዳ መሬት ላይ ተፈጠፈጠች። ፍትህ ሰዎችን ሁሉ በእኩል ማየቷ ቀረና መደባዊ ሆነች። በዚህ አዲሱ ዕይታ መሠረት የላብአደሩ ፍትህ እና የቡርዣው ፍትህ ለየቅል ብቻ ሳይሆን ተቃራኒ ሆነው ተገኙ። ለአንዱ ፍትሃዊ የሆነ ነገር ሁሉ ለሌላው ኢፍትሃዊ ነው። ከወያኔ መምጣት ጋር ደግሞ ፍትህ መሬት ላይ መንደባለሏም በዝቶ ጉድጓድ ተቆፍሮ እጉድጓጉ ውስጥ ተጣለች። በአዲሱ ወያኔ አመጣሽ ዕይታ እያንዳንዱ ዘር (ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ) በየራሱ ጉድጓድ ውስጥ የቀበራት የራሱ ፍትህ አለው። የትግሬ ፍትህ እና የአማራው ፍትህ አይተዋወቁም። አሮምው፣ አደሬው፣ ሶማሌው፣ አፋሩ፣ ሲዳማው፣ ጉራጌው …. እያንዳንዳቸው የየራሳቸው ፍትህ አላቸው። አንዱ ዘንድ ፍትሃዊ የሆነ ሌላው ጋር ፍትሃዊም ሊሆንም ላይሆንም ይችላል። እንደመደብ ትንተናው እርግጠኛ ሆኖ መናገር አይቻልም። በዚህም ምክንያት ነው ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።
<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## የግንቦት 7 የፍትህ፤ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ዋና ፀሃፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በየመን የጸጥታ ሃይሎች ቁጥጥር ስር መዋላቸውን ተከትሎ በአገር ቤትና በውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ቁጣን መቀስቀሱ ታወቀ

አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በየመን ዋና ከተማ በሆነችው ሰንአ በትራንዚት የ 1፡30 ቆይታ አድርገው ወደ ስራ ቦታቸው በሚሻገሩበት ወቅት ሰኔ 16 2014 በየመን የጸጥታ ሃይሎች መታገታቸውን ግንቦት ሰባት የፍትህ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ማስታወቁን ተከትሎ በአገር ቤትና በውጭ አገር በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ቁጣ መቀስቀሱ ታውቋል። የግንቦት 7 ንቅናቄ የድርጅቱ ዋና አመራር የሆኑት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በየመን የጸጥታ ሃሎች መታገታቸውን የአይን እማኞችን ዋቢ በማድረግ ገልጿል። ግንቦት ሰባት ዋና አመራሩ አቶ አንዳርጋቸው ለጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ተላልፎ ሊሰጥብኝ ይችላል የሚል ከፍተኛ ስጋት ውስጥ መውደቁን ተከትሎ በተለይ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የመን ይህንን ታሪካዊ ስህተት እንዳትፈጽም ለማሳሰብና በአስቸኳይ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን እንድትለቅ ጫና ለመፍጠር በተለያዩ የአለም አገራት የተቃውሞ ሰልፍ መጠራቱም ታውቋል።

ግንቦት 7 እንዳስታወቀው የመን አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ለጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ አሳልፋ የምትሰጥ ከሆነና የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ ደግሞ በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ላይ አንዳች አይነት መንፈሳዊም ሆነ አካላዊ ጉዳት ቢያደርሱ ድርጅቱ የበቀል እርምጃ እንደሚወስድ አስጠንቅቋል። ግንቦት 7 በመግለጫው ” አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ለፋሽስቱ የወያኔ አገዛዝ ተላልፎ ቢሰጥ በአካሉና በሕይወቱ ለሚደርሰው ሁሉ የወያኔ ፋሽስቶችን ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑ ከአሁኑ እናስጠነቅቃለን። በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ አካል፣ መንፈስና ሕይወት ላይ የሚደርሰው ማንኛውም ጥቃት ለነፃነታቸው ለመሰዋት ዝግጁ የሚሆኑ እልፍ አዕላፍ ታጋዮችን እንደሚፈጥር ጥርጥር የለንም። በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ አካል፣ መንፈስ እና ሕይወት ላይ ለሚደርሰው ጥቃት ሁሉ በማንኛውም መንገድ በማንኛውም ቦታ የምንበቀል መሆኑንና ብዙ የወያኔ ሹማምንት ዋጋ የሚከፍሉበት እንደሚሆን እንዲያውቁት እናስጠነቅቃለን” ብሎአል።

አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ለማስፈታት የሚደረገውን ግፊት በተጠናከረ ሁኔታ ለማስተባበበርና ለመግፋት ኮሚቴ ተቋቁሞ ስራ መጀመሩ የታወቀ ሲሆን ግንቦት7 ለየመን ፕሬዚዳንት ፊልድ ማርሻል አብዱ ራቡ ማንሱር ሃዲ እኤአ ሰኔ 30፣ 20014 በጻፈው ደብዳቤ የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ መታፈን ህገወጥ በመሆኑ የየመን መንግስት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲፈታው ጠይቋል። የጉጅሌው ወያኔ ተቃዋሚዎቹን፣ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችን፣ ጋዜጠኞችንና አገዛዙን የሚተቹትን ሁሉ አስሮ የሚያሰቃይ መሆኑ በአለማቀፍ ማህበረሰብ ዘንድ የተረጋገጠ መሆኑን በመጥቀስ፣ የየመን መንግስት የአቶ አንዳርጋቸውን ተላልፎ ያለመሰጠት መብቱን እንዲያከብር ጠይቋል።

የግንቦት ሰባት ዋና ጸሃፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ መታሰርን ተከትሎ በርካታ ቁጭትን ያዘሉ አስተያየቶች ለሬዲዮ ክፍላችን እየደረሱን ሲሆን ከነዚህም መካከል;

የአቶ አንዳርጋቸው ፅጌን በየመን መታሰርን ለመቃወም የግንቦት 7 አባል ወይንም ደጋፊ መሆን የለብኝም። ኢትዮጵያዊ መሆኔ ብቻ ይበቃል!

አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ሕዝባቸውን ከመከራ ለማውጣት የራሳቸውን የተደላደለ ኑሮ የሰው፤ ፋሽስቶቹ ፈርዖኖች የገነቡላቸውን የምቾት ዓለም ሳይቀር ለወገናቸው ፍቅር ሲል የናቁ ጀግና ናቸው፡፡ አቶ አንዳርጋቸው ማለት ሁሌም የወገናቸውን ጥቅም የሚያስቀድሙ፤ በእርሳቸው ሞት የሌሎችን ሕይወት የሚያደላድሉ ወገኖቹ ነገ እንዲኖሩ ዛሬውን የሚሰው ለሌላው ጥቅም ሲሉ የሚጎዱትን ጉዳትንም እንደጥቅም የሚቆጥሩ፤ ስለከፈሉት መስዋዕትነት የማይጸጸቱ የነፃነት አርበኛ ናቸው፡፡ የየመን መንግስት አንዳርጋቸውን ለወያኔ ጅቦች አሳልፎ እንደማይሰጠው ተስፋ አደርጋለሁ፣ ቢያደርገው እንኳን ለነጻነት የሚደረገው ትግል መልኩን ቀይሮ፣ እስካሁን ከታየውም በበለጠ በቆራጥነትና አንዳንዴም ጭካኔ በተሞላበት መንገድ ይካሄዳል እንጅ አይደበዝዝም።

ወያኔዎቹ እንዲገነዘቡት የምንፈልገው ጉዳይ ቢኖር እውነተኛ የነፃነት አርበኛ ሊታሰር፤ ሊሞትና ሊሰዋ ይችላል። ነገር ግን ይህ የተጀመረውን ትግል ፈጽሞ ሊገታም ሆነ ሊያቆም ከቶ አይችልም። ኢትዮጵያም አንድ አንዳርጋቸውን ብቻ ሳይሆን ሚሊዮን አንዳርጋቸውን ፈጥራለችና በከንቱ አትድከሙ። ወደዳችሁም ጠላችሁም ድሉ የማታ ማታ የጭቁኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ይሆናል!

የሚሉት ይገኙበታል። ከቡራትና ከቡራን አድማጮቻችን ለሬዲዮ ክፍላችን በስልክ ከአገር ቤትና ከውጭ የደረሱንን በርካታ ቁጭትን ያዘሉ የህዝብ አስተያየቶች በአየር ላይ እንደምናውል በዚህ አጋጣሚ ለማሳሰብ እንወዳለን።

በጉዳዩ ዙሪያ የተለያዩ የፖለቲካ ሃይሎችም መግለጫ በማውጣት ተቃውሞዋቸውን እያሰሙና አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ለፋሽስቱ የወያኔ አገዛዝ ተላልፎ እንዳይሰጥ ለማድረግ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እያበረከቱ እንደሚገኙም ለማወቅ ተችሏል።

## ጥቂት ነጥቦች በፍትህ ጉዳይ ላይ

. . . ( ከገጽ 4 የዞረ )

ማኅበረሰባችን ብዥታ በበዛበት ሁኔታ ላይ የሚገኘው። ለምሳሌ አንዱ ዘር በገነባው ሀውልት በሀሴት ሲጨፍር፤ ሌላው በንዴት ይበግናል፤ ሶስተኛው ደግሞ ምንም ስሜት አይሰጠውም። በአንድ ቋንቋ እየተነጋገርን መሰማማት የቸገረንም በዚህ የፍትህ እሳቤ መዛባት ጭምርም ነው።

### 4. ምልከታ ወደፊት

ይህ ሁሉ የሚያመለክተው (1) አገራችን የምትገኝበት አሳሳቢ ደረጃ፣እና (2) እኛ (ማለትም በዚህ ዘመን ያለነው ኢትዮጵያዊያን) ላይ የወደቀውን የኃላፊነት ክብደት ነው። ዜጎች ፍትህ የማግኘት ተስፋቸው ሲሟጠጥ በሚኖሩበት ማኅበረሰብ ላይ የነበራቸው ተስፋ ይጨልማል። “ታግለን ሥርዓቱን ወደ መልካምነት ልንቀይረው እንችላለን” የሚለው እምነት ካልዳበረ ለሀገር፣ ለወገን፣ ለመጪው ትውልድ መጨነቅ ያቆሙና እያንዳንዱ ሰው “እኔ ምን አቀበጠኝ” እያለ ሁሉም ጭቆናን ችለው ለመኖር ሊመርጡ ይችላሉ። ይህ እንዳይመጣ መወሰን ያለብን በየግላችን ነው።

ይህን ወሳኝ የግል ውሳኔ የሰጠን ሰዎች ደግሞ መሰባሰብና ተግባሮቻችን ማቀናጀት ይኖርብናል። እንዲህ ካደረግን በአገራችን የተንሰራፋውን ኢፍትሃዊነትን መዋጋት የሚቻለው በፓለቲካ ሥርዓቱ ላይ ለውጥ ሲመጣ መሆኑን ለማመን ጊዜ አይወስድብንም። ከዚህ ቀጥሎ የሚመጣው አቢይ ጥያቄ “ለውጥ እንዴት?” የሚለው ይሆናል። ከዚያ በፊት ግን በለውጡ አስፈላጊነት እና ይህ ለውጥ ካልመጣ ሰዎች ሆነን የመቀጠላችን ጉዳይ እንኳን አጠራጣሪ መሆኑ በትክክል ልንረዳ ይገባል። ይህ ቁርጠኝነት ሥር እንዲሰድ ስለ ፍትህ ያለን ግንዛቤ በየጊዜው መዳበር ይኖርበታል።

በፍትህ እጦት ሳቢያ በየእስር ቤቶች እየተሰቃዩ ላሉ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን፤ ከማሳዎቻቸው ተፈናቅለው ለተበተኑ ወገኖቻችን፤ አደገኛ የበረሃና የባህር ጉዞ በማድረግ ለተሰደዱ ወገኖቻችን፣ ለራሳችን እና ለመጪው ትውልድ ልንደርስለት ይገባል። ፍትህን ከተቀበረችበት ጉድጓድ በቶሎ ካላወጣናት አገር አይኖረንም፤ እኛም ሰዎች ሆነን አንቀጥልም። በዚህ የኃላፊነት እና የአጣዳፊነት ስሜት ነው የፍትህ ግንዛቤዓችን መገንባት የሚኖርበት።

*

ፀሐፊውን በ tkersmo@gmail.com ማግኘት ይቻላል